በከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር
የከተሞች ምግብ ዋስትናና ሴፍቲኔት ጽ/ቤት

የአካል ጉዳተኞች በከተማ ሴፍቲኔት ፕሮጀክቶች አካታችነትና ተጠቃሚነት፣ በአፈጻጸም የጋጠሙ ችግሮችና ዘላቂ መፈትሄዎች

መጋቢት፣2017 ዓ.ም

አዳማ

የስነዱ ይዘት

መግቢያ

ዓላማ

በፕሮጀክቱ የተገኙ ውጤቶችና ቀጠይ ስራዎች



በፕሮጀክቱ የአካል ጉዳተኞች አካታችነትና ተጠቃሚነት

በአፈጻጸም የጋጠሙ ችግሮች

ማጠቃለያ

መግቢያ

- ከዓለም ህዝብ 15% ገደማ, ወደ አንድ ቢሊዮን የሚጠጉ ሰዎች በአካል ጉዳተኞች ናቸው ይላል:: 80% የሚሆኑት በታዳጊ አገሮች ውስጥ ይኖራሉ፣
- በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ ወደ 17 ሚሊዮን (17.6%) አካል ጉዳተኞች(PWDs) እንዳሉ ይገመታል፡
- አካል ጉዳተኞች በድህነት ውስጥ እንደሚኖሩ ተነግሯል:: ከዚህ ውስጥ አብዛኛዎቹ የሚኖሩት መሰረታዊ አገልግሎቶች እና ድጋፎች በቂ ባልሆኑባቸው የገጠርና ከተማ አካባቢዎች ናቸው::
- አካል ጉዳተኝነት ከድህነት ጋር ግንኙነት እንዳለው፣ ከትምህርት፣ከጤና፣ ከሥራ፣ ከገቢ እና መሠረታዊ የማህበራዊ አገልግሎቶች ያለማግኘትን ይጨምራል::

የቀጠለ...

- በሃገር አቀፍ ደረጃ የወጡ ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን በማስፈጸም ድህነትን ማስወገድ እንደ ዋና አጀንዳቸው አድርገው በመረባረባቸው ተጨባጭ ለውጦች እየተመዘገቡ ይገኛሉ::

- በከተሞች የሚስተዋለውን የምግብ ዋስትና ችግር ማቃለል እና በዘላቂነት ማስወገድ የከተሞች የምግብ ዋስትና ስትራቴጂ እና የማህበራዊ ጥበቃ ፖሊሲን ለማሳካት እንደ ቁልፍ አጀንዳ ተወስዷል::

- በዚህ መሰረት በከተሞች የዜጎችን ምግብ ዋስትና ማረጋገጥና ድህነትን በዘላቂነት መቅረፍ የከተሞች ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮጀክት ዋና ዓላማ ነው::

የስነዱ ዓላማ

በከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔት ፕሮጀክት የአካል ጉዳተኞች አካታችነትና ተጠቃሚነት፣ በአፈጻጸም የጋጠሙ ችግሮችና ዘላቂ መፈትሄዎች ላይ አውደጥናት ማድረግ ነው።



በፕሮጀክቱ የተገኙ ውጤቶችና ቀጠይ ስራዎች



- በከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔትና ስራ ፕሮጀክት ከ11 ከተሞች ወደ 88 ከተሞች እንዲየድግ ተደርጓል።
- ከ604 ሺ ተጠቃሚዎች ወደ 1.7 ሚሊዮን ዜጎችነን ተጠቃሚዎች አድጓል፣
- ፕሮጀክቱ የኢትዮጵያ መንግስትና የአለም ባንክ በገቡት ስምምነት መሰረት በ$703.5 ሚሊዮን በ88 ከተሞች ወደ 1,7 ዜጎችን ተጠቃሚ ለማድረግ ሰፊ ስራዎች ተሰርቷል።
- በተጨማሪ ለማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ 15 ቢሊዮን ብር ለ699,112 ተጠቃሚዎች ተመድቦ ወደ ስራ ተገብቷል።

የቀጠለ...

- ተጠቃሚዎች ቀልጣፍና ወቅታዊ ክፊያ እንዲያገኙ ተደርጓል።
- ከ1.7 ሚሊዮን ተጠቃሚዎች ውስጥ 58% የሚሆኑት ሴቶች ናቸው።
- ፕሮጀክቱ የዜጎች ኑሮ ከማሻሻል ባለፈም የከተሞች የጽዳት ውበትና የተፋሰስ ልማት ስራ ለማገዝ እና የመሰረተ ልማት ችግሮችን ለመቅረፍ ተጨማሪ አቅም ሆኗል።

የተጠቃሚዎች ቁጥር በየኮሚፖነንቱ ስንመለከት፡-

❑በአከባቢ ልማት፡ - 527,546

❑በቀጥታ ድጋፍ፡ - 163,279

❑በስደተኞች እና ስደተኛ ተቀባይ ማህበረሰብ፡- 124,565



❑በወጣቶች የስራ ላይ ልምምድ : - 62,883

❑ በጎዳና ላይ ተዳዳሪዎች : - 14,000

❑ በሀገር ውስጥ ተፈናቃዮች : - 814,867

በማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ

❑አከባቢ ልማት 587,410 እና በቀጥታ ድጋፍ 111,702 በድምሩ 699,112 ተጠቃሚዎች ወደ ስራ ገብቷል።

የቤተሰቦች መመልመያ መስፈርቶች በተመለከተ

1) ቤተሰቡ ውስጥ ሥራ ለመስራትና ራስን ለማስተዳደር በሚከለክል የአካል ጉዳት ወይም የጠና በሽታ ምክንያት መስራት የማይችል የቤተሰብ አባል መኖር፣
2) የቤተሰቡ አስተዳዳሪ (እማወራ ወይም አባወራ) መደበኛ ትምህርት ያልተማረ መሆን፣
3) የቤተሰቡ አባላት የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ያላጠናቀቁ መሆን፣
4) በእማወራ የሚመራ ቤተሰብ መሆን፣
5) ቤተሰቡ ቋሚ የገቢ ምንጭ የሌላቸው መሆን፣

6) የግል የመኖሪያ ቤት የሌላቸው መሆን፣

7) ቤተሰቡ ካሉት የቤተሰብ አባላት መካከል ራሳቸውን ያልቻሉት ቁጥር ራሳቸውን ከቻሉት የበለጠ መሆን፣ (ከ15 አመት በታች እና ከ60 ዓመት በላይ የሆኑ የቤተሰብ አባላት መብዛት)

8) በእማወራ ወይም አባወራ ብቻ የሚመራ ቤተሰብ መሆን (የትዳር አጋር የሌለው)፣

9) በቤተሰቡ የሚሰራ ፍሪጅ የሌለው መሆኑ፣

10) በቤተሰቡ 14 ኢንች እና ከዚያ በላይ ቴሌቪዥን የሌለው መሆኑ፣


11) በቤተሰቡ የሚሰራ የኤሌክትሪክ የእንጀራ ምጣድ የሌለው መሆኑ፣

በፕሮጀክቱ የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚነት በተመለከተ

ተ.ቁ	ክልል	በፕሮጀክቱ የአካል ጉዳተኞች ተጠቃሚዎች ብዛት			
		ወንድ	ሴት	ድምር	
1	ትግራይ	292	458	750	
2	አፋር	44	28	72	
3	አማራ	1,131	1,692	2,823	
4	ኦሮሚያ	1,714	2,460	4,174	
5	አ.አ	4,095	5,468	9,563	
6	ለደቡብ ኢትዮጵያ	1,469	1,816	3,285	
7	ማዕከላዊ ኢትዮጵያ	466	672	1,138	
8	ሲዳማ	286	262	548	
9	ሶማሌ	760	230	990	
10	ሀረር	53	80	133	
11	ድሬዳዋ	203	88	291	
12	ቤ/ጉሙዝ	46	39	85	
13	ደ/ምዕራብ ኢትዮጵያ	235	266	501	
14	ጋምቤላ	88	58	146	
ጠቅላለው ድምር		10,882	13,617	24,499	

የቀጠለ...

- በከተሞች ልማታዊ ሴፍቲኔትና ስራ ፕሮጀክት ከ24,499 በላይ አካል ጉዳተኞች ተጠቃሚ ሆኖል፣
- በፕሮጀክቱ ከ11ዱ የተጠቃሚ ቤተሰቦች የመምረጫ መስፈርቶች ውስጥ አንዱ በአካል ጉዳት ምክንያት መስራት የማይችል የቤተሰብ አባል መኖር የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያደርጋል።
- መስራት የሚችል ቤተሰብ አባል ያላቸው አካል ጉዳተኞች የአካባቢ ልማት ተጠቃሚ ሆኖል፣
- በፕሮጀክቱ የአካል ጉዳተኞች አካታችነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የተጠቃሚዎች ምልመላ እና ቅሬታና አቤቱታ አፈታት ሂደት ውስጥ በየቀበሌና ቀጠና የአካል ጉዳተኞች ተወካይ እንዲሳተፉ ተደርጓል።



የቀጠለ...




- የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የአካል ጉዳተኞች መብቶች ኮንቬንሽን አንቀጽ 9 መሰረት አካል ጉዳተኞች ኑሯቸውን በነፃነት እንዲመሩና ያልተገደበ ተሳትፎ እንዲያደርጉ የማስቻልና የፕሮጀክቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

- የአካል ጉዳተኞች የዘላቂ ኑሮ ማሻሻያ ተጠቃሚ እንዲሆነ ለማድረግ የፕሮጀክቱ ማለፊጸሚያ ማኑዋል የማሻሻል ስራ ተሰርቷል።

- በመንግስት ማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ ተከትሎ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙ ዜጎች በተለየ አካል ጉዳተኞች የማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ተደርጓል።

የቀጠለ...



- መንቀሳቀስ ለማይችሉ አካል ጉዳተኞች በፕሮጀክቱ የሚሰጠውን ገንዘብ በወቅቱ እንዲያገኙ ከንግድ ባንክ ጋር በትስስር እየተሰራ መሆኑ፣
- አካል ጉዳተኞች ከወርሃዊ ክፊያ በተጨማሪ መሰረታዊ ማህበራዊ አገልግሎቶች ማለት የጤና፣ የትምህርት፣ የስነ-ልቦና ድጋፍ፣ የህግ አገልግሎት በነጻ እንዲያገኙ ተደርጓል።
- በማህበረሰቡ አቀፍ ጥምረት (CCC) ጋር በመሆን የቤት ጥገና እና ሌሎች አቅርቦቶች ተጠቃሚ ሆኖል።
- አካል ጉዳተኞች በመስፈርቱ መሰረት በፕሮግራሙ ማካተት እና ተደራሽ እንዲሆኑ ተደርጓል።

የቀጠለ...

- በአካል ጉዳት ምክንያት አልጋ ቁራኛ የሆኑ ተጠቃሚዎችን በሶሻል ወርኬሮች አማካኝነት በየግዘው ቤት ለቤት ክትትልና ድጋፍ ተደርጓል።
- ከድህነት ወለል በታች እና አነሰተኛ የገቢ ያላቸውን አካል ጉዳተኞች በሌሎቹ በተለየ መልኩ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው ጥረት ተደርጓል።



- ፕሮጀክቱ በተቻሌ መጠን የአካል ጉዳተኞች አካታችነትና ተጠቃሚነት እንዲረጋገጥ ጥረት ተደርጓል።
- አካል ጉዳተኞች ከፕሮጀክቱ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በየወር ክፊያ እንዲያገኙ ተደርጓል።

በአፈጻጸም የጋጠሙ ችግሮች

- እንደ ሀገር የአካል ጉዳተኞች መረጃ በትክክል የመያዝና የመረጃ አስተዳደር ስርዓት አለመኖር፣
- በፕሮጀክቱ የአካል ጉዳተኞችን አካታችነትና ተጠቃሚነት የሚያረጋገጥ ጋይድላይን አለመኖር፣
- የአካል ጉዳተኞች በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ አካታችነትና ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በባለድረሻ አካላት መካከል ጠንካራ ትብብር እና አጋርነት አለመኖር፣
- በፕሮጀክቱ የአከባቢ ልማት ስራ ላይ መሳተፍ ለሚፈልጉ አካል ጉዳተኛ ተጠቃሚዎች ረዳት መሳሪያዎችን አልማመቻችት፣

ዘላቂ መፈትሄዎች



- የህብረተሰቡን አመለካከት ለውጥ ማምጣት እና በአካል ጉዳተኞች ላይ በራስ መተማመን ለመፍጠር መስራት፣
- የአካል ጉዳተኞች መረጃ በትክክል የመያዝና የማጥራት እንዲሁም የመረጃ አስተዳደር ስርዓት ማቋቋም፣
- የአካል ጉዳተኞች ማህበራዊ ድህንነት እንዲጠበቅ የማህበራዊ ጥበቃ ስትራቴጂና ፖሊሲን ማጠናካር፣

የቀጠለ...



- አካል ጉዳተኞችን በተለያዩ ፕሮግራም ውስጥ ማካተት እና የአካል ጉዳተኛ ማህበራትን አቅም መገንባት፣
- በፕሮጀክቱ የአከባቢ ልማት ስራ ላይ መሳተፍ ለሚፈልጉ አካል ጉዳተኛ ተጠቃሚዎች ረዳት መሳሪያዎችን ማመቻችት፣
- መንግስት፣ የሲቪክ ማህበራት፣ ማህበረሰቡ እና ሌሎች የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት አካል ጉዳተኞችን በተለያዩ ፕሮግራም ውስጥ የማካተትና የመተግበር ሂደት ማጠናከር፣

አመሰግናለሁ!!!